# የአርበኞች ግንቦት 7 ድምጽ

የአርበኞች ግንቦት 7፣ ለአንድነትና ዲሞክራሲ ንቅናቄ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

የአርበኞች ግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 351 ጥር 22


የኢትዮጵያ የጦርና የፖሊስ ሠራዊት አባላት በግል ከሚደርስባችሁ ግፍ በተጨማሪ የገዛ ራሳችሁን ወገኖች መግደላችሁ፣ ማቁሰላችሁ፣ ማድማታችሁና መደብደባችሁ የህሊና እረፍት ሊነሳችሁ ይገባል። ህሊናችሁ እረፍት የሚያገኘው የሥርዓቱ እድሜ ሲያጥር መሆኑን በመገንዘብ ለገዛ ራሳችሁ ክብር፣ ለወገናችሁና ለአገራችሁ ስትሉ ፋሽስቱን ወያኔ ከድታችሁ ከአርበኞች ግንቦት 7 ኃይል ጋር ተቀላቀሉ።

ከአርበኞች ግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## MI- 35 ተዋጊ ሄሊኮፕተር ይዘዉ ወያኔን የከዱት የአየር ሃይል ባልደረቦች በመልካም ሁኔታ ላይ እንደሚገኙ ታወቀ

ከአንድ ወር በፊት በታህሣሥ 10 ቀን 2007 ዓ.ም. ከድሬዳዋ የአየር ኃይል ምድብ የጦር ልምምድ ላይ የነበሩት ሁለት ከፍተኛ የጦር ሄሊኮፕተር አብራሪዎች እና አንድ ቴክኒሻን የፋሺስቱ ህወሓት አገዛዝን በመክዳት MI -35 የተሰኘ ዘመናዊ የጦር ሄሊኮፕተር ይዘው ወደ ሶስተኛ አገር በማቅናት ጥገኝነት መጠየቃቸው በኢትዮጵያውያን ዘንድ ሰፊ መነጋገሪያ ሆኖ መሰንበቱ የሚታወስ ሲሆን በአሁኑ ሰአት ሶስቱ የአየር ሃይል ባልደረቦች በመልካም ሁኔታ ላይ እንደሚገኙ የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን (ኢሳት) ዘገበ። ግለሰቦቹ ሻምበል ሳሙኤል ግደይ፣ ሙቶ አለቃ ቢልልኝ ደሳለኝ እና ቴክኒሻን ጸጋ ብርሃን ግደይ እጅግ በተረጋጋ እና በጥሩ ሁኔታ ላይ እንደሚገኙ በመረጃው የተገለጸ ሲሆን በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚደረገው የነጻነት ትግል አስተዋጽኦ ለማድረግ መዘጋጀታቸውን ግለሰቦቹ ለኢሳት ተናግረዋል። ሶስታችንም በአንድ ላይ የምንመደብበትን ጊዜ ስንጠብቅ ቆይተን ነበር ያሉት ፓይለቶቹ፣ አጋጣሚው ሲፈጠርላቸው ቀደም ብሎ ባወጡት እቅድ መሰረት መጥፋታቸውን ገልጸዋል። በሙያቸው ከፍተኛ ልምድና ችሎታን በማካበት አንቱታን ያተረፉት ሁለቱ አብራሪዎችና አንድ ቴክኒሻን ለምን ወጣችሁ ተብለው ከኢሳት ለቀረበላቸው ጥያቄ ፓይለቶቹ ሲመልሱ፣ በአየር ሃይል ውስጥ የተንሰራፋው ዘረኝነት፣ አድልዎና የአስተዳደር መበላሸት ይህን ውሳኔ እንዲወስኑ እንዳስገደዳቸው ገልጸዋል። አያይዘውም እድሉን ቢገኙ አብዛኛው የአየር ሃይል አባላት አገዛዙን ከድተው ለመውጣት ዝግጁ መሆናቸውን ገልጸዋል። ፓይለቶቹ ሁኔታዎችን አመቻችተው ለኢሳት ቃለምልልስ እንደሚሰጡ መናገራቸውን ለማወቅ ተችሏል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ዘረኛውን የህወሓት አገዛዝ በመክዳት ከጭቁኑ ህዝብ ጎን የተሰለፉት 3 ቱ የአየር ሃይል ባልደረቦች በሰሩት ጀብዶ የኢትዮጵያ ህዝብ ድጋፍና ክብሩን ለፓይለቶቹ የገለፀ ..... ( ወደ ገጽ 3 ዞሯል )

## በዝዋይ ወህኒ ቤት በእስረኞች ላይ የሚፈጸመው አረመኔያዊ ጥቃትና የሰብአዊ መብት ጥሰት ተባብሶ የከፋ ደረጃ ላይ መድረሱ ታውቀ

*በወህኒ ቤቱ ቅጥረኛ አረመኔ ገራፊዎች በሚደርሰበት ተደጋጋሚ ጥቃት በመማረሩ አንድ ወጣት ሁለት አይኖቹን በምላጭ ቆራርጦ ማጥፋቱ ታውቋል።*

በዝዋይ ወህኒ ቤት ታስሮ የሚገኘውና በጨካኞቹ የህወሃት ቅጥረኛ ገራፊዎች በተደጋጋሚ በሚደርስበት የከፋ ስቃይና ድብደባ የተማረረው ሞገስ መካሻ የተባለ ወጣት በጥር 5 ቀን 2007 ኢ.ም ሁለት አይኖቹን በምላጭ ቆራርጦና ወጋግቶ ማጥፋቱን ለማወቅ ችለናል። የወህኒ ቤቱ ገራፊዎች ዘወትር ከምሽቱ 4 ጀምሮ የተለያዩ ታሳሪዎችን እየወሰዱ ከፍተኛ ድብደባና ማሰቃየት እንደሚፈጽሙባቸው ታውቋል። አንዳንድ ጊዜ በታሳሪዎች ላይ ድብደባው በቀን ጭምር እየተፈጸመባቸው እንደሚገኝ ለማወቅ የተቻለ ሲሆን አብዛኞቹ ታሳሪዎች የሰብአዊ መብቶቻቸውን በሚጥስ ሁኔታ በቤተሰቦቻቸው እንዲሁም በወዳጆቻቸው እንዳይጎበኙ መከልከላቸውንና ጥቂት በማይባሉት ላይ ደግሞ ማጉላላት እየተፈጸመባቸው እንደሚገኝ ለማወቅ ችለናል።በዝዋይ ወህኒ ቤት በእስረኞቹ ላይ ከሚፈጸመው ጥቃት ባሻገር በተለይ ልዩ የጥበቃ ክፍሎች ተብለው በሚጠሩትና እነ ጀነራል ማሞ ታስረው በሚገኙበት ስፍራ የህክምና ክትትል የሚያስፈልጋቸው እስረኞች ሳይቀር መብታቸው ተነፍጎ ህክምና ተከልክለው በከፍተኛ ስቃይ ውስጥ እንደሚገኙም ለማወቅ ችለናል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ኮረኔል ደምሰው አንተነህና ኮረኔል ደምሰው አለሙ የተባሉ የእድሜ ልክ እስራት የተፈረደባቸው መኮንኖች ታህሳስ 27 ቀን 2007 በዚሁ ወህኒ ቤት በህወሃት ቅጥረኞች በጥይት መደብደባቸውን መዘገባችን የሚታወስ ነው።

## የፋሽስቱ ወያኔ በአንድነት ፓርቲ አመራሮችና ደጋፊዎች ላይ የወሰደው አረመኔያዊ እርምጃ ኢትዮጵያውያንን ማስቆጣቱ ታወቀ

የፋሺስቱ ወያኔ አገዛዝ ባሳለፍነው እሁድ በአዲስ አበባ ከተማ ለተቃውሞ ሰልፍ በወጡ የአንድነት ፓርቲ አባላትና ደጋፊዎቹ ላይ የወሰደው አሰቃቂ የሃይል እርምጃ በኢትዮጵያውያን ዘንድ ከፍተኛ ቁጣ መፍጠሩን ለማወቅ የተቻለ ሲሆን የአገዛዙ ውንብድ ያስቆጣቸው ኢትዮጵያውያን በተለይ ከአብራተኛው አገዛዝ ትዕዛዝ በመቀበል አረመኔያዊ ድብደባዎችንና ግፎችን በህዝብ ላይ እየፈጸሙ ለሚገኙ የፖሊስ አባላት ከድርጊታቸው እንዲቆጠቡ ቁጣ የተቀላቀለበት ጥሪ እያስተላለፉ እንደሚገኙ ታውቋል። ፖሊስ የህዝብን ደህንነት ለመጠበቅ የሚሰራ አካል እንጂ የአንድ አምባገነን ቡድን ሹምባሽ መሆን የለበትም የሚሉት ኢትዮጵያውያኑ በሰልጠና ወቅት የገቡትን ቃለ መሃላ መጠበቅ አለባቸው፤ ለህዝብ መከታ ሆነው መቀጠል ይኖርባቸዋል ሲሉ አሳስበዋል። የፋሺስቱ ወያኔ ቅጥረኛ ፖሊሶች በሰልፈኞቹ ላይ በወሰዱት የሃይል እርምጃ አንድ የሰባት ወር እርጉዝ ሴትን ጨምሮ ከ 30 በላይ ሰዎች ላይ ከፍተኛ ድብደባ የፈጸሙ ሲሆን አሰቃቂ ድብደባ የተፈጸመባቸው ተጎጅዎች አሁን ድረስ በጤና ተቋማት ህክምና እየተከታተሉ እንደሚገኙ ለማወቅ ችለናል። ይህ በእንዲህ እንዳለ የአብራተኛው ወያኔ የሃይል እርምጃ ዕያደረጉት ካለው የነፃነት ትግል አንድ ኢንች እንኳ ፈቀቅ ሊያደርጋቸው እንደማይችል የገለጸው አንድነት ፓርቲ በአዲስ አበባ እና በአንዳንድ የክልል ከተሞች የሚደረግ ድጋሚ የተቃውሞ ሰልፍ ለመጭው እሁድ ጥር 24/ 2007 አም መጥራቱ ታውቋል። በተቃውሞ ሰልፎቹ ህዝብ በነቂስ ወጥቶ እንዲሚሳተፍባቸው ይጠበቃል።

## ወያኔ አንድነትንና መኢአድን አፍርሶ እንደገና በአምሳሉ ፈጠራቸዉ

የቦርዱ ሰብሳቢ ፕሮፌሰር መርጋ በቃና እና የቦርዱ ጸሀፊና ጽ/ቤት ሃላፊ አቶ ነጋ ዱፌሳ በጋራ ዛሬ ጥር 21 ከቀኑ 10፡00 ሰአት በአዲስ አበባ ሒልተን ሆቴል በሰጡት መግለጫ በእነአቶ በላይ ፍቃዱ የሚመራው አንድነት፤ የፓርቲውን ደንብና የምርጫ አዋጁን የጣሱ ተግባራትን እንደሚያከናውን፣ ፓርቲው ያካሄደውን ጉባዔ ለሰባት ወራት ሳያሳውቀው መቆየቱ፣ የቀድሞ ፕሬዚደንት ከሃላፊነታቸው የተነሱት ሕጉን ጠብቆ አለመሆኑን፣ ፓርቲው ለሁለት ሲከፈል ቦርዱ ልዩነታቸውን በጋራ ለጠቅላላ ጉባዔ አቅርበው እንዲያስወስኑ ቢጠይቅም ፈቃደኛ ሆነው አለመገኘታቸውን ጠቅሰዋል።

በአንጻሩ የአንድነት ፓርቲን ሕግና ደንብ አክብረው ተንቀሳቅሰዋል፣ ጠቅላላ ጉባዔ አካሄደዋል ላላቸው ለአቶ ትግእስቱ አወል ቡድን ዕውቅና እንዲሰጥ ቦርዱ በዛሬው እለት ባካሄደው ስብሰባ በሙሉ ድምጽ ወስኖል ብለዋል። ቦርዱ በመግለጫው፣ የፓርቲውን ህልውና ለማስቀጠልና ወደ ምርጫ የሚገባ ፓርቲ ስለሚያስፈልግ፣ የእነ አቶ በላይ በፈቃዱ ቡድን በርካታ የህግ ጥሰቶችን የፈጸመና እየፈጸመ የሚገኝ በመሆኑ በሌላ በኩል ደግሞ የእነ አቶ ትእግስቱ አወሉ ቡድን ህግን በማክበር ለመንቀሳቀስ ጥረት እያደረገ ያለ በመሆኑ፣ ይህንን ፓርቲ ለመምራት ቦርዱ እውቅና ሰጥቷል ብሎአል። እነ አቶ ትእግስቱ አወሉ አንድነትን በመምራት ወደ ምርጫው እንዲገቡ ፈቃድ መስጠቱን ቦርዱ አስታውቋል። ...... ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## አንድነት በመጪው እሁድ የጠራው ሰልፍ ውጥረት ፈጥራል

ፓርቲው ባወጣው መግለጫ ህወሃት/ኢህአዴግ ጥር 17/2007 ዓም በአንድነት አመራሮችና አባላት ላይ ያደረሰውን አሰቃቂ ድብደባ ለማውገዝ እንዲሁም ፓርቲውን ለመቀማት የሚደረገውን ጥረት ለማውገዝ ለጥር 24 በአዲስ አበባና በሌሎች የተለያዩ የክልል ከተሞች ላይ ሰልፍ ለማድረግ ማቀዱን ገልጿል። አምባገነኑ የህወሀት/ኢህአዴግ መንግስት የዘንድሮውን ሀገራዊ ምርጫ ሂደቱንም ጭምር በማበላሸት ጠንካራ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ከምርጫው ውጪ እንዲሆኑ ለማድረግ ላይ ታች እያለ ነው የሚለው አንድነት ፓርቲ፣ በምርጫ ቦርድ፣ በኢቲቪ እና በሬዲዮ ፋና የሶስትዮሽ ግንባር በመክፈት በህዝቡ ዘንድ ብዥታ እንዲፈጠር፣ ምርጫው ያለጠንካራ ተዋዳደሪ እንዲካሄድ በማድረግ የምርጫውን ዋጋ ቢስነት አረጋግጧል ብሏል።

አንድነት ፓርቲ በአዲስ አበባ ለሚካሄደው ሰልፍ ደብዳቤ ማስገባቱን የፓርቲው የህዝብ ግንኙነት ሃላፊ አቶ አስራት አብርሃ ገልጿል። መስተዳድሩ በእለቱ የአፍሪካ ህብረት ስብሰባ መኖሩን ገልጾ ሰልፉን አለመፍቀዱን ቢያስታውቅም፣ አንድነት ፓርቲ የመስተዳድሩን ሃሳብ አለመቀበሉን አቶ አስራት አክለው ገልጸዋል። በሌላ በኩል ደግሞ ምርጫ ቦርድ የምዝገባ ጣቢያዎች በሰዎች ድርቅ በተመቱበት በዚህ ወቅት ይመዘገባል ...... ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## የሰላም በሮች ሲዘጉ የሁለገብ ትግል ስልት በሮች ይከፈታሉ!!!

አንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ በምርጫ ቦርድ አማካይነት እየደረሰበት ያለውን በደል ለሕዝብ ለማሰማት ጥር 17 ቀን 2007 ዓም በአዲስ አበባ፣ ደብረ ማርቆስ፣ ጂንካና ሸዋ ሮቢት የተቃውሞ ሰልፎችን ጠርቶ ነበር። በተለይ በአዲስ አበባው ሰልፍ ላይ የተገኙ ወገኖቻችን ለህወሓት ፍጹም ታማኝ በሆነው የፓሊስ ክፍል ያለርህራሄ መደብደባቸው እና የተቃውሞ ሰልፉም በጉልበት መበተኑ ነፃነትና ፍትህ ናፋቂውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ያሳዘነ ብቻ ሳይሆን ያስቆጨ ጉዳይ ነው። በመላው ዓለም በሚደረጉ የተቃውሞ ሰልፎች ላይ የተለመደውን ድንጋይ ውርወራ እንኳን ሳይከጅሉ፤ የፓሊሶችን ሰብዓዊ ርህራሄ ለማግኘት “ፓሊስ የኛ ነው” እያሉ እየዘመሩ በፓሊስ ተደበደቡ። ሴቶችና አዛውንት ብቻ ሳይሆን ተላላፊ መንገደኞች እንኳን ከፓሊስ ዱላ አላመለጡም። ከሁሉም በላይ የሚዘገንነው ደግሞ የ 7 ወራት ነብሰ ጡር ሴትም በፓሊስ መመታትዋና ሆዷ መረገጡ ነው። ይህ እኩይ ተግባር የሚፈጥረው ቁጭት በህወሓት ላይ ብቻ አያበቃም። ትዝብቱ ለፓሊስም ተርፏል። ይህ የጭካኔ ተግባር ለፍትህና ለነፃነት በሚደረገው ትግል የሕዝብ አጋር ይሆናል ተብሎ ተስፋ የተጣለበት የፓሊስ ሠራዊትን የሚያዋርድ ነው። ደካማ እናቶችን፣ አረጋዊያንን፣ ባዶ እጃቸውን ተቃውሞ እያሰሙ ያሉትን ወጣቶችንና ነፍሰጡሮችን በጭካኔ መደብደብ ለራሱና ለሥራው ክብር ለሚሰማው ፓሊስ ውርደት ነው፤ የሞት ሞት ነው። የኢትዮጵያ የፓሊስ ሠራዊት አባላት ተግባራቸው ያሳፍራቸዋል፣ ይቆጫቸዋል፤ ቁጭታቸውንም ይህን ትዕዛዝ በሰጡ አለቆቻቸው ላይ በግልም ሆነ በተደራጀ መንገድ በሚወስዱት እርምጃ እናያለን ብሎ የኢትዮጵያ ሕዝብ ተስፋ ያደርጋል።

የጥር 17 ቀን 2007ቱ ሽብር በአንድ ወቅት የተፈጠረ፤ በአንድነት ፓርቲ ላይ ብቻ ያነጣጠረ፣ የተናጠል ክስተት ሳይሆን ህወሓት ደግሞ ደጋግሞ ሲፈጽመው የነበረ ነው። ከዚህ በፊት በሙስሊም ወገኖቻችን ላይ ፈጽሞታል። የአዲስ አበባ ከተማ ማስተር ፕላንን በተቃወሙ የተለያዩ ዩንቨርስቲዎች ተማሪዎች በተለይም በአምቦ ላይ የብዙዎችን ሕይወት የቀጠፈ ሽብር ነዝቷል። በቅርቡ ደግሞ በሰማያዊ ፓርቲ አባላት ላይ ተመሳሳይ አረመናዊ ድርጊት ፈጽሟል።

አርበኞች ግንቦት 7: ለአንድነትና ዲሞክራሲ ንቅናቄ፣ የህወሓት ታጣቂዎች በወገኖቻችን ላይ ያደረሱትን ድብደባ፣ ህገወጥ እስር፣ እና የተቃውሞ ሰልፍ ክልከላን አጥብቆ ይቃወማል። አርበኞች ግንቦት 7፣ በወገኖቻችን ላይ የደረሰው ህመም ህመሙ፣ ቁስላቸው ቁስሉ ነው።

ባለፉት ሃያ ሶስት ተከታታይ ዓመታት፣ በአምቦ፣ በጅማና በኦሮሚያ የተለያዩ ከተሞችና ገጠሮች፣ በባህዳር፣በጎንደርና በበርካታ የአማራ ከተሞችና ገጠሮች፣ በጋምቤላ፣ በሶማሊ፣ በአፋር፤ በአጠቃላይ በመላው ኢትዮጵያ በየአስፋልቱ፣ በየሜዳውና በየጥሻው በህወሓትና ተላላኪዎቻቸው የፈሰሰው የኢትዮጵያውያን ደም በከንቱ ፈሶ መቅረት የለበትም ብሎ አርበኞች ግንቦት 7 በጽኑ ያምናል። አርበኞች ግንቦት 7 ከሌሎች መሰል ድርጅቶች ጋር በመተባበር የህወሓትን እድሜ በማሳጠር የእናቶቻችን እምባ ሊያብስ ዝግጁ ነው። አርበኞች ግንቦት 7 ኢትዮጵዊያን እንደከብት እየተደበደቡ ወደ ማጎሪያ የሚያጋዙበት እና በጠገቡ ሰላዮችና ፓሊሶች እየታነቁ የሚታረዱበት ጊዜ ማብቃት አለበት ይላል።

የቱን ያህል ቢለመንም ሆነ ቢወገዝ ህወሓት ለነፃ፣ ፍትሃዊና ተዓማኒን ምርጫ ዝግጁ ሊሆን ቀርቶ በምርጫ የሚወዳደሩት ፓርቲዎች እነማን እንደሆኑና እነማን በእጩ ተወዳደሪነት መቅረብ እንዳለባቸው ሳይቀር የሚወስን ዓይን አውጣ አጭበርባሪ ድርጅት ነው። ይህንን ከዚህ በፊት አይተነዋል፤ አሁንም በአንድነትና በመኢአድ ላይ እየተደገመ ነው። ህወሓት፣ በየአምስቱ ዓመታቱ በሚያደርጋቸው የሴራ ምርጫዎች በሚቀጥሉት አርባና ከዚያም በላይ ለሆኑ ዓመታት በሥልጣን ላይ የሚቆይበትን ስልት ቀይሶ የሚንቀሳቀስ፤ ኢትዮጵያን ለብዙ ዓመታት ለመግዛት ማድረግ የሚችለውን ክፋት ሁሉ ከማድረግ የማይመለስ አገር በቀል ቅኝ ገዥ ነው። ህወሓት የዘረጋው ሥርዓት ህገ-አልባነት፣ ፀረ-ሕዝብነት እና አምባገንነት ለማጋለጥ በሚል ርህራሄን በማያውቁ የሥርዓቱ አገልጋዮች ፊት ባዶ እጅ መጋፈጥ የሚፈጥረው የሞራል የበላይነትና የመንፈስ ጀግንነት ባያጠራጥርም የሚያስከፍለው ዋጋ ከሚገኘው ውጤት ጋር ማመዛዘን ግን እጅግ ተገቢ የሆነ የማይታለፍ ሥራ ነው ብሎ አርበኞች ግንቦት 7 ያምናል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ከህወሓት የሴራ ምርጫ ፋይዳ ያለው ውጤት ይገኛል ብሎ አይጠብቅም። ከምርጫው የሚፈልገው ውጤት አንድ ነገር ብቻ ነው፤ እሱም የመንግሥት ለውጥ ነው። ምርጫው በምርጫነቱ ወደ መንግሥት ለውጥ አያደርስም፤ ወደ መንግሥት ለውጥ ወደሚያመራ ሕዝባዊ አብዮት ሊያሸጋግር ግን ይችላል። ይህም ቢሆን የኢትዮጵያን ተጨባጭ ሁኔታ በተለይም የሠራዊቱን ዓይነትና አደራጀጀት እግምት ውስጥ ባስገባ ሁኔታ መታቀድ ይኖርበታል።

አርበኞች ግንቦት 7 የራሱን ጥናት አድርጎ ለኛ አገር ተጨባጭ ሁኔታ እና ህወሓትን ለመሰለ ጠላት የሚመጥን የትግል ስልት ሁሉንም የትግል ስልቶች እንደሁኔታው ያዳቀለ - ሁለገብ - መሆን ይኖርበታል ብሎ ወስኖ ለተግባራዊነቱ እየተንቀሳቀሰ ነው። ሁለገብ የትግል ስልት ሕዝባዊ ተቃውሞን፣ ሕዝባዊ እምቢተኝነትንና ሕዝባዊ አመጽን እንደወቅቱ ተጨባጭ ሁኔታ ማፈራረቅና ማደባለቅን ይፈልጋል። ሰላማዊ ትግል በተለይም ሕዝባዊ እምቢተኝነት ሲባል ደግሞ ህወሓት ያወጣቸው አፋኝ ህጎች እያከበሩ የሚደረግ አለመሆኑም የኢትዮጵያ ሕዝብ ይረዳል። ሁለገብ ትግል በተቻለ መጠን የወገን ኃይል ራሱን ፈጽሞ መከላከል በማይችልበት ሁኔታ እንዳይገኝ ለማድረግ ይጥራል። በአርበኞች ግንቦት 7 እምነት ሁለገብ የትግል ስልት ሰፊ ተቀባይነት የሚያገኝበት ወቅት ደርሷል። ከዚህ በፊት “የሰላም በሮች ሲዘጉ የአመጽ በሮች ይከፈታሉ” ተብሎ በአንድ ታዋቂ ኢትዮጵያዊ ታጋይ የተነገረው “የሰላም በሮች ሲዘጉ የሁለገብ ትግል ስልት በሮች ይከፈታሉ” በሚል እንዲሻሻልና በዚህ ወለል ብሎ በተከፈተው በር ሁላችንም እንድንገባ አርበኞች ግንቦት 7 ያሳስባል። በሁለገብ የትግል ስልት በሰላማዊ መንገድ የሚደረጉ የትግል ዓይነቶች አሉ፤ በሌላም መንገድ የሚደረጉ አሉ። ስለሆነም በሁለገብ ትግል እያንዳንዳችን እንደየዝንባሌዓችንና እንደየችሎታዎቻችን አስተዋጽኦ ልናበረክት የምንችልበት ሰፊ እድል ይከፍትልናል።

ስለሆነም፣ በዚህ አጋጣሚ አርበኞች ግንቦት 7፣ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ ለጦር ሠራዊትና ፓሊስ አባላት ወገናዊ ጥሪ ያደርጋል።

በህወሓት ዘረኛ አገዛዝ በሚደርስብን ውርደት፣ እንግልት፣ ስደት፣ ሥራ አጥነትና ድህነት የተማረራችሁ እና እኩልነቷ የተረጋገጠ፣ የበለፀገች ኢትዮጵያን ማየት የምትመኙ ሁሉ የሁለገብ የትግል ስልትን አዋጪነት እንድታጤኑ የዚሁ ስልት አካል ሆናችሁ እንድትታገሉ አርበኞች ግንቦት 7 ጥሪ ያደርጋል።

የኢትዮጵያ የጦርና የፓሊስ ሠራዊት አባላት በግል ከሚደርስባችሁ ግፍ በተጨማሪ የገዛ ራሳችሁን ወገኖች መግደላችሁ፣ ማቁሰላችሁ፣ ማድማታችሁና መደብደባችሁ የህሊና እረፍት ሊነሳችሁ ይገባል። ህሊናችሁ እረፍት የሚያገኘው የሥርዓቱ እድሜ ሲያጥር መሆኑን በመገንዘብ ለገዛ ራሳችሁ ክብር፣ ለወገናችሁና ለአገራችሁ ስትሉ ፋሽስቱን ወያኔ ከድታችሁ ከአርበኞች ግንቦት 7 ኃይል ጋር ተቀላቀሉ።

እነዚህን ጥሪዎች ተግባራዊ ካደረግን ወገኖቻችን መሠረታዊ መብቶቻቸውን በመጠየቃቸው በመወደስ ፋንታ በፓሊስ ዱላ ሲደበደቡ የማናይበት ዘመን ይመጣል። ይህ ካልሆነ ግን “ውሀና መብራት አጣን” ብሎ አቤቱታ ማሰማት እንኳን በጥይት የሚያስገድልበት ቀን ይመጣል። ያ ከመሆኑ በፊት እንወስን፤ ራሳችንና አገራችን ከህወሓት ዘረኛ አገዛዝ ነፃ እናውጣ።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

## ወያኔ የጋረደብንን የመበታተን አደጋ ለማክሸፍ ትግላችንን ማቀናጀትና በአንድ የአመራር ጥላ ሥር ማሰባሰብ ወቅቱ የሚጠይቀን እርምጃ ነው

ትግራይን ከተቀረው የአገራችን ክፍል ለመገንጠልና የትግራይን ሪፑፐሊክ ለማቋቋም ራዕይና ተልዕኮ ሰንቆ የዛሬ 40 አመት ደደቢት በረሃ ውስጥ የተፈጠረው ህዝባዊ ወያኔ ሃርነት ትግራይ፡ በለስ ቀንቶት የመንግሥት ሥልጣን ከተቆጣጠረ ወዲህ፡ በስሙ የሚነግድበትን የትግራይን ህዝብ ጨምሮ በአገራችንና በመላው ህዝባችን ላይ የፈጸማቸው ወንጀሎችና ያደረሳቸው ሰቆቃዎች ተዘርዝረው የሚያልቁ አይደሉም።

ከነዚህ ወንጀሎች ሁሉ የከፋውና ምናልባትም የሚቀጥለውን ትውልድ ጭምር ዋጋ ያስከፍላል ተብሎ የሚፈራው ምዕራባዊያን ቅኝ ገዥዎች አህጉራችን አፍሪካን በተቀራመቱበት ወቅት የአገዛዝ ዘመናቸውን ለማራዘምና ቅኝ የገዙዋቸውን ህዝቦች ሃብትና ንብረት ለመዝረፍ እንዲመቻቸው የተጠቀሙበትን የከፋፍለህ ግዛ ፖሊስ በምድራችን ተግባራዊ በማድረግ ለዘመናት የተገነባውን የህዝብ አንድነትና የአገር ሉአላዊነት ሊያናጋ በሚችል መልኩ በዘር፤ በቋንቋና በሃይማኖት ተከፋፍለን የጎሪጥ እንድንተያይ የተፈጸመብን ደባ ነው።

በዚህ ደባ ምክንያት ዛሬ በአገራችን ታሪክ ታይቶና ተሰምቶ በማይታወቅ ሆኔታ ኦሮሞነት፤ ሱማሌነት፤ ትግሬነት፤ አማራነት ፤ ስዳማነት፤ አፋርነት፤ ወላይታነት ፤ ከምባታነት ወዘተ ከዘግነት በላይ ገዝፎ የማንነት መለያና የፖለቲካ፤ የኢኮኖሚና ማህበራዊ መብቶች መሠረት ሆኖአል። በዚህም የተነሳ የኦሮሞ ከብት አርቢ ለከብቶቹ ግጦሽ ፍለጋ ወደ ሱማሌ ድንበር ከተሻገረ እንደ ባዕድ ተቆጥሮ ተኩስ ይከፈትበታል፤ አፋር ወደ ኢሳ ከተሻገረ ይገደላል፤ ለቤነሻንጉል በተከለለ ክልል የሰፈረ የአማራ አርሶ አደር የደከመበትን አንጡራ ሃብት ተቀምቶ ይባረራል፤ አኝዋክ ለዘመናት ተከባብሮና ተቻችሎ ከኖረው ከኑዌር ወንድሙ ጋር እንዲጋጭ ተደርጎ በገላጋይነት ሥም የፌደራል ፖልስና የጸጥታ ሃይል በጅምላ እንዲጨፈጭፈው ይፈረድበታል። በመልካም አስተዳደር እጦት የደረሰበትን መከራና ስቃይ አብሮ ሲጋፈጥ የኖረው የወልቃይት ጠገደ ህዝብ አንተ አማራ አንተ ትግሬ በሚል የዘር ክፍፍል ለመገዳደል ካራውን ስሎ ተቀምጦአል ። ይህ አልበቃ ብሎም የአንድ ብሄር አባላትን በጎሳ ሸንሽኖ የጉጂ ኦሮሞ ከአርስ ወንድሙ ጋር ደም እንዲቃባ ተደርጎአል። የኦጋዴን የተለያዩ ጎሳዎችም ላይ እንዲሁ።

ወያኔ በጉልበት የጫነብን የመከፋፈልና የመለያየት አደጋ አንድ ቀን ሲያበቃ የነጻነት ብርሃን ፈንጥቆ በሠላምና በመቻቻል የምንኖርበት አገር እንኳ እንዳይኖረን በተለያዩ የአገራችን ክፍሎች መጠነ ሰፊ የሆነ ድንግል መሬታችንን ለህንድ፤ ለቻይናና ለአረብ ከበርቴዎች በርካሽ ዋጋ በመቸብቸብ በገዛ አገራችን የባዕዳን አሽከሮች ሆነን እስከ ዘለአለሙ እንድንኖር መሠረት ተጥሎአል።

ይህ ሁሉ በደልና መከራ እንዲያበቃ በአገዛዙ ላይ የተቃውሞ ድምጹን ያሰማ ከሥራውና ከኑሮው ተፈናቅሎ በድህነት አረንቋ ውስጥ እንዲጣል አለያም እየታደነና የሽብርተኝነት ታፔላ እየተለጠፈበት ወደ የማጎሪያ ጥቢያዎች እንዲወረወር ተደርጎአል። በዘርና በቋንቋ በተከለለልን ክልል በፈረቃ የሚደርስብንን አፈናና ሰቆቃ በህብረት ለመቃወም የሚደረጉ ጥረቶች በሙሉ "የቀድሞ ሥርዓት ናፋቂ፤ ትምክህተኛ ፤ አክራሪ/ጽንፈኛ፤ ጸረ ልማት ወዘተ " በሚሉ የማሸማቀቂያና የመወንጀያ ቃላቶች ጋጋታ እንዲደናቀፍ ለማድረግ ተሞክሮአል።

ግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄና የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር ጥር 2 ቀን 2007 አመተ ምህረት የፈጸሙት ውህደት ዋናው ምክንያት ከላይ የተዘረዘሩትን ግፎች ለማስቆም በተናጠል ከሚደረግ ትግል በህብረት የሚደረገው ትግል ያለው ጠቀሜታ ከፍተኛ መሆኑ የፈጠረው ግንዛቤ ነው ። የወያኔ የጥቃት ክንዶች የፈረጠሙት በራሱ ጥንካሬ ወይም የሚተማመንበት ህዝባዊ ድጋፍ በደጀንነት ኖሮት ሳይሆን በኛ መከፋፈልና መለያየት ብቻ እንደሆነ ህዝባችን ከተረዳው ውሎ አድሮአል።

አርበኞች ግንቦት 7 በሚል መጠሪያ ሁለቱ ድርጅቶች በቅርቡ የፈጠሩት ውህደት ከድህረ ምርጫ 97 ጀምሮ ህዝባችን ከደረሰበት ስቆቃ ለመገላገል ተቃዋሚዎችን "ተባበሩ ወይም ተሰባበሩ" በማለት ሲያቀርብ ለኖረው የድረሱልኝ ጥሪ የተሰጠ የመጀመሪያው ተግባራዊ ምላሽ ነው። ሁለቱም ድርጅቶች እስከ ዛሬ ምድር ላይ ያደራጁትን የሰው ሃይል ፤ እውቀትና ንብረት አዋህደው በአንድ አመራር ሥር ትግሉን ከዳር ለማድረስ መወሰናቸው በአላማና ግብ ለሚመስሉዋቸው ሌሎች ተቃዋሚ ሃይሎች ብቻ ሳይሆን ወያኔን ከህዝብ ጫንቃ ላይ በማውረድ ፍትህና እኩልነት በአገራችን እንዲሰፍን እንታገላለን ለሚሉት ሃይሎች ሁሉ አርአያነት ያለው እርምጃ መሆኑ እየተነገረ ነው ። የአርበኞች ግንቦት 7 ውህደት በተፈጸመበት ሥነሥርዓት ላይ አገራቸውን ነጻ ለማውጣት ነፍጥ አንግበው ከሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች ውስጥ የትግራይ ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ [ዴሚት] ሊቀመንበር አቶ ሞላ አስግዶም ፣ የአፋር ነጻነት ግንባር [አርዱፍ] ሊቀመንበር አቶ ኢብራሂም ሙሳ ፤የጋምቤላ ህዝብ ነጻነት ንቅናቄ [ጋህነን] ሊቀመንበር አቶ ኦኬሎ አይዴድ ፣ የቤነሻንጉል ተወካይና የአድሃን ተወካዮች በየተራ የተናገሩት በአንድ የጋራ ግንባር ሥር ተሰባስቦ በገንዘብና በመሣሪያ ብዛት ተብቶ የህዝባችንን መከራና ስቃይ እድሜ እያራዘመ ያለውን የጥቂቶች አገዛዝ በሃይል የማንበርከክ አስፈላግነትና ወቅታዊነት ሁለቱ ድርጅቶች የፈጸሙት ውህደት ለትብብር ፈር ቀዳጅ መሆኑን አመላክቶአል ። አገራችንን ከመበታተን አደጋ ለመታደግ ወያኔ ባወጣቸው የአፈና ህጎች ተገዝተን ለውጥ ማምጣት አንችልም ያልን ሃይሎች እየተዋሃድንና እየተጣመርን በሄዱን ቁጥር አፈናና እንግልት ተቋቁመን እንታገላለን ያሉት ሃይሎችም በተናጠል ከሚደርስባቸው ጥቃት ለመገላገል ሲሉ ወደ ውህደትና ጥምረት ጎዳና ማቅናታቸው የማይቀር ነው።

ህዝባችን ላይ የደረሰው ግፍና መከራ ጳዋ ሞልቶ እየፈሰሰ ባለበት በዚህን ሰዓት የአገሩ ጉዳይ አሳስቦት በፖለቲካ ድርጅቶች ዙሪያ የተሰባሰበ ወገን ሁሉ ለመቀራረብና ለመተባበር እያደረገ ያለው ጥረት ተስፋ ሰጪና አበረታች ሆኖአል። በዚህ አጋጣሚ ላለፉት 24 አመታት ወያኔ በወገኖቻችን ላይ ለፈጸማቸው ሰቆቃዎች በመሣሪያነት ያገለገሉና እያገለገሉ ያሉ ወገኖች በሙሉ ከውህዱ አርበኞች ግንቦት 7 የአንድነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ አንድ የተላለፈላቸው ወገናዊ ጥሪ አለ። ይህም ጥሪ **እስከ ዛሬ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ወይም ለሥራ ዋስትና ብላችሁ የዚህ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ መሳሪያ በመሆን በወገኖቻችሁ ላይ ግዲያ ፤ እስርና ግርፋት ስትፈጽሙ የኖራችሁ ሁሉ የበደላችሁትን ህዝብ ለመካስ የአገዛዙን ዕድሜ ለማሳጠር በምናደርገው የሞት ሽረት ትግል ላይ እንቅፋት ከመሆን እራሳችሁን አግልሉ** ! የሚል ነው። ትግላችን ወሳኝ የታሪክ ምዕራፍ ላይ ገና ከመድረሱ ከህዝብ በዘረፉት ሃብትና ገንዘብ ልጆቻቸውንና ቤተሰቦቻቸውን ወደ ባህር ማዶ ማሸሽ ለጀመሩት ስግብግብ አለቆችህ ምቾትና ድሎት ብለህ ይህ የመከራ ዘመን ሲያልፍ በሃላፊነት የሚያስጠይቅህን ወንጀል ለነጻነት በሚታገሉ ወገኖችህ ላይ እንዳትፈጽም ለአገር የመከላኪያ ሠራዊት፤ ለፖልስና የጸጥታ ሃይል አባላት ሁሉ ጥሪ ቀርቦአል።

የጊዜ ጉዳይ ካልሆነ በቀር ድል ማድረጋችንን ፈጽሞ የማንጠራጠር የነጻነት ታጋዮች በሙሉልብ የምንናገረው ወያኔ አገራችንን ለመበታተን የቻለውን ሁሉ ድንጋይ ቢፈነቅልም በአንድ የአመራር ጥላ ሥር ተሰባስበን አገራችንን ከተጋረጠባት የመበታተን አደጋ ለመታደግና እያንዳንዱ ዜጋ የሚኮራባት የበለጸገችና ሉአላዊነቷ የተረጋገጠ አገር ባለቤት ለመሆን የጀመርነው ትግል ግቡን እንደሚመታ ነው። ለዚህ ደግሞ በቅርቡ የፈጸምነው ውህደትና ከሌሎች ጋር በጥምረት ጠላትን ለመፋለም የጀመርነው ተግባራዊ እንቅስቃሴ ወቅታዊነት ለወገን ተስፋ ለጠላት መርዶ ነው።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ !**

## MI- 35 ተዋጊ ሄሊኮፕተር ይዘዉ ወያኔን የከዱት የአየር ሃይል

... ( ከገጽ 1 የዞረ )

ሲሆን ጀግና በማለትም ክብርና ውዳሴ አጎናጽፏቸዋል። ጀግኖቹ የጦር ሄሊኮፕተር አብራሪዎቹ ይዘውት ወደ ሶስተኛ አገር የተሻገሩት የ MI- 35 የጦር ሄሊኮፕተር ከ 35 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር በላይ ዋጋ እንደተገዛ የውስጥ ምንጮቻችንን ዋቢ በማድረግ መዘገባችን አይዘነጋም።

በሌላ ዜና ባለፉት 6 ወራቶች ብቻ የዘረኛው ህወሓትን አየር ሃይል በመክዳት ወደ ጎረቤት አገር ኤርትራ በማቅናት በአካባቢው የሚንቀሳቀሱ መሳሪያ ያነሱ የነፃነት ሃይሎችን የተቀላቀሉ ኢትዮጵያውያን ቁጥር ከ 11 በላይ መሆኑ መዘገባችን የሚታወስ ሲሆን ከዚህ ጋር በተያያዘ የአየር ሃይል ህልውና አደጋ ውስጥ በመውደቁ በዘረኞቹ ህወሓቶች መንደር ከፍተኛ ድንጋጤ መፈጠሩን መዘገባችን አይዘነጋም። ከዚህ ጋር ተያይዞ በአየር ሃይል ተቋም ውስጥ የደረሰውን ከባድ ኪሳራ እንዲሁም በተቋሙ ላይ የተደቀነውን የመፈራረስ አደጋ ለማስተባበል ዘረኞቹ የህወሃት ቱባ ሹማምንት የተለያዩ ዲስኩሮችን ሲያሰሙ መከረማቸው አይዘነጋም።

.........

## ወያኔ ከምርጫው በፊትም ሆነ በኋላ አፈናውን ያቆማል የሚል ተስፋ የለኝም ሲል ሂውማን ራይተስ ዋች አስታወቀ

ድርጅቱ ባወጣው የ2014 አለማቀፍ የሰብአዊ መብት አያያዝ ሪፖርት ላይ እንደጠቀሰው መንግስት ጋዜጠኞችን፣ ጸሃፊዎችን እና የተቃዋሚ ፓርቲ ደጋፊዎችን እንደፈለገ ያስራል፣ በሰላም ተቃውሞአቸውን ለመግለጽ በወጡ ዜጎች ላይ ፖሊስ የሃይል እርምጃ ይወስዳል፤ እንዲሁም ለማፈኛነት እየዋሉ ያሉትን በአለማቀፍ ማህበረሰብ ዘንድ የተወገዙትን አዋጆችን ለመለወጥ ምንም ምልክት አላሳየም ብሎአል።

ባለፈው አመት የኢትዮጵያ መንግስት ማንኛውንም ተቃውሞ ለማፈን መሞከሩን የገለጹት የሂውማን ራይትስ ወች የአፍሪካ ምክትል ዳይሬክተር ሌስሌ ሌፍኮው፣ ጋዜጠኞችና ተቃዋሚዎች ከሁሉም በባሰ እንደተሰቃዩና ከመጪው ምርጫ በፊት ሁኔታዎች ይሻሻላሉ የሚለው ተስፋ ሙሉ በሙሉ እንደተዳፈነ ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ እየፈጸመች ያለችው አስከፊ የሰብአዊ መብት ጥሰትን የለጋሽ አጋራትን አለመተቸታቸውን ሂውማን ራይትስ ወች በሪፖርቱ አመልክቷል። ሰማያዊ ፓርቲ የተቃውሞ ሰልፎችን እንዳያደረግ መከልከሉ፣ በኦሮምያ ክልል በሚያዚያና ግንቦት ወሮች የጸጥታ ሃይሎች ከፍተኛ ጉዳት ማድረሳቸው፣ የግንቦት7 ዋና ጻሀፊ አቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ህገወጥ በሆነ መንገድ የመን ውስጥ ተይዘው መሰጠታቸውና የታሰሩበት ቦታ አለመታወቁንም ገልጿል። ዞን 9 እየተባሉ የሚጠሩ ጸሃፊዎች በጸረ ሽብር ህግ መከሰሳቸውን፣ የ6 ጋዜጣ አሳተሚዎች በተመሳሳይ ወነጀል መከሰሳቸውን የጠቀሰው ሂማውን ራይትስ ወች፣ መንግስት ዌብሳይቶችን መዝጋቱን እንዲሁም ስልኮችን በመጥለፍ መረጃዎችን እንደሚያሰባሰብ አትቷል።

በኦሞ ሸለቆ አካባቢ በርካታ ዜጎች ያለፍላጎታቸውና ተገቢው ካሳ ሳይከፈላቸው እንደሚፈናቀሉም ድርጅቱ አስታውቋል። መንግስት ተደጋጋሚ ወቀሳና ትችት ቢደርስበትም የጸረ ሽብር ህጉንና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ለመቆጣጠር የወጣውን ህግ ለመቀየር ፈቃደና አለመሆኑን የጠቀሰው ሂውማን ራይትስ ወች፣ የመንግስትን የልማት እቅድ የተቹ ሰዎች እስራትና ወከባ እንደሚያጋጥማቸው አትቷል።መንግስት ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ መብትን ማፈኑ በመጪው ምርጫ ላይ አሉታዊ ተጽኖ እንደሚኖረው ሌስሌ ሌፍኮው ተናግረዋል። ሂማን ራይትስ ወች በ656 ገጽ ሪፖርቱ በአለም ዙሪያ ያሉ የ90 አገራት የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን ቃኝቷል።

## “የለውጥ ሀይሎች ያለን አማራጭ እንደሰው መኖር ወይም መብትን ለማስከበር እስከመጨረሻው መጽናት ነው” ጋዜጠኛ ስለሽ ሀጎስ

በትናንቱ የአንድነት ሰላማዊ ሰልፍ ላይ በፖሊሶች ከፍተኛ ብትር ያረፈበትና የአካል ጉዳት የደረሰበት ጋዜጠኛ ስለሽ ታሞ በተኛበት ከኢሳት ጋር ባደረገው አጭር ቆይታ ትናንት እንደሱ የከፋ በትር ላረፈባቸው የትግል አጋሮቹ እና ለለውጥ ሀይሎች በሙሉ “አይዟችሁ! እንበርታ! መብታችንን ለማስከበር ከምናደርገው ትግል በፍጹም ወደ ሁዋላ እንዳንል፤ 2007 የለውጥ ዓመታችን ነው” ሲል መልእክት አስተላልፏል።

በሰልፉ ላይ እንዴት እና በምን እንደተመታ እንዲሁም መመታቱን ተከትሎ የሆነውን ነገር እንደማያስታውስ የተናገረው ጋዜጠኛ ስለሽ፤ ደብዳቢዎቹ ከላይ በታዘዙት መሰረት እሱንና የተወሰኑ አጋሮቹን ተመዳድበው ኢላማ ውስጥ ሳያስገቧችወ እንዳልቀረ ጥርጣሬ አለው።

ጓደኞቹ ወደ ሆስፒታል ወስደውት በተደረገ የራጅ ምርመራ በተለይ የእጆቹ አጥንቶች እንደተሰባበሩና ከፍተኛ ኦፐሬሽን መደረግ እንዳለበት በሀኪሞች የተነገረው ስለሽ፤ የፊታችን ሐሙስ ኦፐሬሽን እስከሚደረግ ድረስ ለጊዜው በጀሶ ታጅሎለት ተኝቶ ይገኛል።በእጁ ላይ ከደረሰበት ስብራት በተጨማሪ ፊቱን ጭምሮ በመላ አካሉ ላይ ከባድ ቅጥቀጣ ደርሶበታል። “ ይሁንና ይህ ድበድባና ዱላ እኔን፣ ጓደኞቼንም ሆነ የለውጥ ሀይሎችን ከትግላችን አይገታንም” ብሏል-ስለሽ

ነፍስ ጡሯን የፓርቲውን አባል ጨምሮ አንድነት ፓርቲ ትናንት እሁድ በቀበና በጠራው ሰልፍ ላይ የወጡ በርካታ ሰዎች በፖሊሶች ክፉኛ መደብደባቸውና ጥቂት የማይባሉ ታፍሰው ወዳልታወቀ ቦታ መወሰዳቸው ይታወቃል። ሁላችንም የለውጥ ሀይሎች ያለን አማራጭ ሁለት ነው፤ አንደኛው እንደሰው መኖር ነው፤ ይህ ካልሆነ መብትን ለማስከበር እስከመጨረሻው መጽናት ነው”ሲል ጋዜጠኛ ስለሽ ሀጎስ ገለጸ። ጓደኞቹ ወደ ሆስፒታል ወስደውት በተደረገ የራጅ ምርመራ በተለይ የእጆቹ አጥንቶች እንደተሰባበሩና ከፍተኛ ኦፐሬሽን መደረግ እንዳለበት በሀኪሞች የተነገረው ስለሽ፤የፊታችን ሐሙስ ኦፐሬሽን እስከሚደረግ ድረስ ለጊዜው በጀሶ ታጅሎለት ተኝቶ ይገኛል።

በእጁ ላይ ከደረሰበት ስብራት በተጨማሪ ፊቱን ጭምሮ በመላ አካሉ ላይ ከባድ ቅጥቀጣ ደርሶበታል። “ይሁንና ይህ ድበድባና ዱላ እኔን፣ ጓደኞቼንም ሆነ የለውጥ ሀይሎችን ከትግላችን አይገታንም” ብሏል። ስለሽነፍስ ጡሯን የፓርቲውን አባል ጨምሮ አንድነት ፓርቲ ትናንት እሁድ በቀበና በጠራው ሰልፍ ላይ የወጡ በርካታ ሰዎች በፖሊሶች ክፉኛ መደብደባቸውና ጥቂት የማይባሉ ታፍሰው ወዳልታወቀ ቦታ መወሰዳቸው ይታወቃል።

## የ9ኙ ፓርቲዎች ትብብር -አንድነት አባላት ላይ የተወሰደውን የጭካኔ እርምጃ በጥብቅ አወገዘ

ትብብሩ ባወጣው አስቸኳይ መግለጫ፤ ገዥው ፓርቲ በአንድነት የውስጥ ጉዳይ ገብቶ የሚፈፅመውን ደባ ለመቃወም ሰልፍ በወጡ የአንድነት አመራሮች፣ አባላት፣ ደጋፊዎችና በፓርቲው ጽህፈትቤት ፊት ለፊት በሚገኘው ቤተ ክርስትያን አካባቢ በነበሩ አዛውንቶቸ ላይ ሳይቀር ድብደባ በመፈጸም ፤ጭካኔውን ዳግመኛ አሳይቶናል ብሏል።

ትብብሩ ጠርቶት በነበረው የአዳር ሰላማዊ ሰልፍ ላይ የተወሰደውን ዘግናኝ እርምጃ ያስታወሰው መግለጫው፤”የ9ኙ ፓርቲዎች ትብብር አብሮ ስለመስራትና ሌሎቹም ትብብሩን እንዲቀላቀሉ በየጊዜው የሚወተውተው አገራችን በዚህ ዘመን በማይመጥን አምባገነንና የጭካኔ ስርዓት ውስጥ የምትገኝ መሆኑን በመረዳቱ ነው።” ብሏል። “ስርዓቱ በሰላማዊ ዜጎች ላይ አሁንም የጭካኔ እርምጃውን መድገሙ ስልጣኑን የማጣት ከፍተኛ ስጋት ውስጥ እንዳለ እና ከይስሙላ ላለፈ ለሰላማዊ ትግሉ ዝግጁ አለመሆኑን የሚያሳይ ነው።” ያለው ትብብሩ፤ “የስርዓቱን ጨካኝነት እያወቁም ቢሆን በራሱ በስርዓቱ የማይከበረውን ህገ መንግስታዊ መርህ ተከትለው ሰልፍ ለወጡት ቆራጥ የአንድነት አመራሮች፣ አባላትና ደጋፊዎች ትብብራችን አድናቆቱን መግለጽ ይወዳል።” ብሏል።

“መስዋዕትነታችሁ ለነገ ድላችን ስንቅ በመሆኑ ይበልጡን ተጠናክራችሁ በጋራ ትግላችን እንደምናጠናክርም እምነታችን ነው።” ያለው ትብብሩ በተቃራኒው ገዥው ፓርቲ ህግ የማክበርና የማስከበር ሚናውን ረስቶ በአንድነት አመራሮች፣ አባላትና ደጋፊዎች ላይ የፈፀመውን ለዘመኑ የማይመጥን የጭካኔ እርምጃ በጥብቅ እናወግዛለን።” ብሏል። “ኢትዮጵያውያንን የማስተዳደር አቅምና ሞራል ያጣው ገዥው ፓርቲ የዜጎችን ጥያቄ በኃይል ማዳፈን የማይቻል መሆኑንና አገራችንን ወደባሰ ችግር እንደሚከታት ተረድቶ ከዚህ የጭካኔ እርምጃው እንዲቆጠብ፣ እርምጃውን የወሰዱት አካላት በህግ ተጠያቂ እንዲሆኑና የታሰሩትን በአስቸኳይ እንዲፈቱ እናሳስባለን።” ብሏል ትብብሩ።

በመጨረሻም “ፖሊስ፣ ደህንነት፣ መከላከያና ሌሎች ተቋማት ገዥው ፓርቲ አላፊ መሆኑን በመገንዘብና ከገዥው ፓርቲ ታዛዥነት በመውጣት ወገኖቻችሁ ላይ እንዲህ አይነት የጭካኔና አሳፋሪ እርምጃ ከመውሰድ ተቆጥባችሁ ከህዝብ ጎን እንድትቆሙ ጥሪያችን እናቀርባለን።” ሲል መግለጫውን ደምድሟል።

### የአርበኞች ግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።

<u>መካከኛ ሞገድ</u>:- በ 358 MB, በ 837 kHz
አ<u>ጭር ሞገድ</u>:- በ 31 MB በ 9700 KHz
**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**
**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሚም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

<u>ማሳሰቢያ</u>:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታስቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

## ወያኔ አንድነትንና መኢአድን አፍርሶ እንደገና

... ( ከገጽ 1 የዞረ )

መኢአድንም በተመለከተ በአቶ ማሙሸት የሚመራውን ቡድን በ2003 ዓ.ም ከፓርቲው አባልነት የተሰረዙ፣የ አባልነት መዋጮ ያልከፈሉ መሆናቸውን፣ ጠቅላላ ጉባኤ ሲያካሂዱም የቦርዱ ተወካይ ያልተገኘ ነበር በሚል ለቀድሞ ፕሬዚደንት ለአቶ አበባው መሐሪ ዕውቅና ይገባቸዋል ሲል ወስኖአል። መኢአድን በተመለከተ ደግሞ የእነ አቶ ማሙሸት አማረ ቡድን የምርጫ ህጉን የጣሱ በመሆኑ እውቅና አይገባቸውም በማለት አቶ አበባው መሃሪ የመኢአድ መሪ ሆነው በምርጫው እንዲሳተፉ ወስኗል።

የአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮ ጋዜጠኛው አቶ መለስካቸው አምሃ " የእነ አቶ ትእግስቱ አወሉ ቡድን በአብዛኛው አባላት ለመመረጣቸው ማስረጃ አላችሁን? መራጮችስ የአንድነት አባላት መሆናቸው በምን ይታወቃል?" በሚል ላቀረበው ጥያቄ፣ የምርጫ ቦርድ ሊቀመንበር ፐ/ር መርጋ በቃና " ሁለቱን ቡድኖች ግድፈቶች እንዳሉባቸውና የማመዛዘን ስራ መሰራቱን እንዲሁም ለቦርዱ ታዛዥ ለሆነው አካል መወሰኑን ተናግረዋል።

ጉዳዩን በማስመልከት ጥያቄ የቀረበላቸው የአንድነት ፓርቲ የህዝብ ግንኙነት ሃለፊ አቶ አስራት አብርሃ፣ ድርጅቱን ለማፍረስ ፖለቲካዊ ውሳኔ መሰጠቱን ገልጸው፣ ስራ አስፈጻሚውና ምክር ቤቱ ተሰብስቦ ውሳኔ እንደሚአሳልፍ አክለዋል ቀደም ሲል ቦርዱ ሁለቱ ፓርቲዎች ችግሮቻቸውን በጋራ ጠቅላላ ጉባኤ አካሂደው እንዲፈቱ መመሪያ የሰጠ ሲሆን ይህ ባለመፈጸሙ አሁንም በድጋሚ በጋራ ስብሰባውን እንዲያካሂዱ የሁለት ሳምንት ጊዜ መስጠቱ ይታወሳል። ሆኖም በጋራ ስብሰባው ባልተካሄደበት ሁኔታ ለአንድ ወገን ዕውቅና መስጠቱ ውሳኔው ፖለቲካዊ እንደሚያደርገው ጉዳን የተከታተሉ ወገኖች እየገለጹ ነው።

የቦርዱ ሰብሳቢ ከመግለጫው በሁዋላ አንድ ጥያቄ ብቻ ተቀብለው ሌላ አልቀበልም በማለት ተቻኩለው አዳራሹን ለቀው ወጥተዋል። ፕሮፌሰሩ መግለጫ በሚሰጥበት ወቅት የመደናገጥና ያለመረጋጋት ስሜት ፊታቸው ላይ ይነበብ ነበር።  አንድነት ፓርቲ የተሰጣቸው የእነ ትግስቱ ቡድን፣ እንዲሁም መኢአድ የተሰጣቸው የእነ አበባው መሃሪ ቡድን በአሁኑ ወቅት ሁለቱንም ፓርቲዎች ወክሎ ጽ/ቤት ከሚገኘው የፓርቲ አመራር ጋር አለመግባባት በመፍጠራቸው በውጭ የሚገኙ መሆናቸው ይታወቃል።

## አንድነት በመጪው እሁድ የጠራው ሰልፍ

... ( ከገጽ 1 የዞረ )

ብሎ ከሚጠብቀው 35 ሚሊየን መራጭ ውስጥ ባለፉት 14 ቀናት ብቻ ከ28 ሚሊየን በላይ ተመዘገበ ማለቱ አነጋጋሪ ሆኗል።

አንድነትና መኢአድ በምርጫ ቦርድ በተሰራባቸው ሴራ ምክንያት በመጪው ምርጫ የመሳተፋቸው ነገር አጠራጣሪ ሆኖአል። በመጪው ረቡዕ ወይም ሐሙስ ምርጫ ቦርድ ፓርቲዎቹን ባስቀመጥኩት ቀነ ገደብ መሰረት ማሟላት የሚገባቸውን ነገሮች አላሟሉም በሚል ከምርጫ ተሳትፎ የሚያግድበትን እርምጃ ሊወስድ እንደሚችል መረጃዎች ያመለክታሉ ።የአንድነት ፓርቲ ለእሁድ ጥር 24 በደሴ ለሚያካሄደው ሰልፍ ከከተማው አስተዳዳር እውቅና ያገኘ ሲሆን ፤ የአዲስ አበባው ግን እያወዛገበ ይገኛል።ከፓርቲው ጽህፈት ቤት የወጣው መረጃ እንደሚያሳየው በደሴ ሰልፉ አራዳ አከባቢ ከሚገኘው የአንድነት ቢሮ ተነስቶ ሆጤ አደባባይ ይጠናቀቃል።

ከ2: 00 ሰ ዓት እስከ 7:00 ሰዓት በሚቆየው በዚህ ሰልፍ፤ የደሴና የአከባቢዋ ህዝብ በነቂስ በመውጣት ምርጫ ቦርድና ገዥው ፓርቲ በ አንድነት ላይ እየፈጸሙት ያለውን ደባ ያወግዛል ተብሎ ይጠበቃል። አንድነት በመጪው እሁድ በአዲስ አበባ ፣ በባህርዳር፣ በደብረታቦር እና በሌሎች የክልል ከተሞች ላይ ሰልፍ ለማድረግ በእንቅስቃሴ ላይ እንደሆነ አሳውቋል። አንድነት በአዲስ አበባ በኩባ አደባባይ ለሚያደርገው ሰልፍ መስተዳድሩን ያሳወቀ ቢሆንም፤ እስካሁን ድረስ ከመስተዳድሩ ምንም ምላሽ አልተሰጠውም።

በሀገሪቱ ህግ መሰረት አንድ አካል ሰልፍ ለማድረግ አሳውቆ በ48 ሰዓት ውስጥ በቂ ምላሽ ካልተሰጠው ያ ሰልፍ ህጋዊ እንደሆነ ይቆጠራል። ይሁንና እስካሁን ለፓርቲው ምላሽ ያልሰጠው የአዲስ አበባ አሰተዳደር “ወደ መዲናዋ እንግዶች ስለሚመጡ ሰልፍ አይደረግም” በማለት ለሌሎች አካላት መናገሩ ተሰምቷል። የኢሳት ምንጮች አንድነት ያስገባውን የሰልፍ ማሳወቂያ ደብዳቤ ተከትሎ በ አዲስ አበባ መስተዳድር ሰራተኞች መካከል አለመግባባት መፈጠሩን ጠቁመዋል።